# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## የ6ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና

## ሒሳብ 2015ዓ.ም/ 2023 እኤአ

**የጥያቄ ብዛት**: 30 **የተፈቀደው ሰዐት**: - 1 ሰዐት

**አጠቃላይ ትዕዛዝ**

ይህ ሒሳብ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዐት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ኢ-ተጋማሽ ሙሉ ቁጥር የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 852 ሐ. 625

ለ. 584 መ. 456

2. ከሚከተሉት ውስጥ ለ9 ተካፋይ ያልሆነው ሙሉ ቁጥር የትኛው ነው?

ሀ.

4824 ሐ. 9486

ለ. 7562 መ. 9695

3. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 12 የ144 አካፋይ ነው። ሐ. 9 የ72 አካፋይ ነው።

ለ. 6 የ108 አካፋይ ነው። መ. 7 የ143 አካፋይ ነው።

4. ከሚከተሉት ቁጥሮች መካከል ብቸኛ ሙሉ ቁጥር የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 43 ሐ. 49

ለ. 81 መ. 63

5. ከሚከተሉት መካከል የ160 ብቸኛ ትንትን የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. $2^4 * 5$ ሐ. $2^3 * 5^2$

ለ. $2^5 * 5$ መ. $2^4 * 5^2$

6. ከሚከተሉት መካከል የ72 እና የ48 ትልቁ የጋራ አካፋይ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ.18 ሐ. 24

ለ. 12 መ. 16

7. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዜሮ የማንኛውም ሙሉ ቁጥር ብዜት ነው።

ለ. 5 እና 7 የ35 አንጻራዊ ብቸኛ ቁጥሮች ናቸው።

ሐ. የ16፣ 18 እና 24 ትንሹ የጋራ ብዜት 144 ነው።

መ. የ15፣ 20 እና 25 ትንሹ የጋራ ብዜት 250 ነው።

8. ሶልያና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ልደቷን ለማክበር ሶስት ቀለማት ያላቸውን አምፑሎች ገዝታ በተመሳሳይ ሰዓት አበራቻቸው። አረንጓዴው በየ12 ሰከንድ፣ ቢጫው በየ18 ሰከንድ እንዲሁም ቀዩ በየ20 ሰከንድ ቢጠፉና ቢበሩ፤ ከስንት ሰከንድ በኋላ ሶስቱም በአንድ ላይ ይበራሉ?

ሀ. 180 ሰከንዶች

ለ. 120 ሰከንዶች

ሐ. 160 ሰከንዶች

መ. 200 ሰከንዶች

9. ከሚከተሉት ውስጥ የ$\frac{81}{36}$ ዝቅተኛ ሂሳባዊ ክፍልፋይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{3}{2}$

ለ. $\frac{9}{2}$

ሐ. $\frac{9}{4}$

መ. $\frac{18}{4}$

10. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. $7\frac{1}{2} = 7.5$

ለ. $5\frac{3}{4} = 5.75$

ሐ. $\frac{4}{5} = 80\%$

መ. $\frac{12}{16} = 70\%$

11. ከሚከተሉት መካከል ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $0.05 = 50\%$

ለ. $0.425 = 42.5\%$

ሐ. $1.015 = 115\%$

መ. $0.205 = 205\%$

12.ከሚከተሉት መካከል ከ75% ጋር እኩል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. $0.75$

ለ. $\frac{3}{4}$

ሐ. $\frac{75}{100}$

መ. $\frac{5}{6}$

13. ከሚከተሉት ክፍልፋዮች መካከል ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል የተቀመጠው የትኛው ነው?

ሀ. $\frac{5}{6}$፣ $\frac{3}{4}$ ፣$\frac{9}{10}$ እና $\frac{2}{5}$

ለ. $\frac{2}{5}$፣ $\frac{3}{4}$ ፣$\frac{5}{6}$ እና $\frac{9}{10}$

ሐ. $\frac{9}{10}$ ፣ $\frac{2}{5}$ ፣ $\frac{5}{6}$ እና $\frac{3}{4}$

መ. $\frac{5}{6}$፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{2}{5}$ እና $\frac{9}{10}$

14. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 85 ሴትና 75 ወንድ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ የወንድ ተማሪዎች ብዛት ከስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል መቶኛ ይሆናል?

ሀ. 46.875%

ለ. 53.125%

ሐ. 48.235%

መ. 47.875%

15. ከሚከተሉት መካከል የ $\frac{3}{4} + 2\frac{4}{5} + 0.25$ ድምር ውጤት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 1.8 ሐ. 3.8

ለ. 2.8 መ. 4.8

16. ሰሎሜ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ልደቷን ለማክበር ቤተሰቦቿ $3\frac{5}{6}$ ኪሎ ግራም ሙዝ፣ 2 ኪሎ ግራም ብርቱካንና $\frac{1}{4}$ ኪሎ ግራም ከረሚላ ገዙላት። በአጠቃላይ ሰሎሜ ለልደቷ ስንት ኪሎ ግራም ምግቦች ተገዙላት?

ሀ. 3 ሐ. 5

ለ. 4 መ. 6

17. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{48}{5} - 9.6 = 0$ ሐ. $8.25 - 5\frac{6}{4} = 1.75$

ለ. $\frac{24}{5} - 1\frac{3}{2} = 2.5$ መ. $3\frac{4}{5} - 3\frac{2}{5} = 0.4$

18. የእንጦጦ ተራራ ከፍታ 3200 ሜትር ሲሆን የዝቋላ ተራራ ከፍታ 2988.75 ሜትር ነው። በእንጦጦ እና በዝቋላ ተራራ መካከል ያለው የከፍታ ልዩነት ምን ያህል ነው?

ሀ. 211.25 ሜትር ሐ. 210.75 ሜትር

ለ. 111.25 ሜትር መ. 215.25 ሜትር

19. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. $2\frac{2}{5} * 4.5 = 10.8$ ሐ. $2\frac{2}{5} * \frac{9}{2} = 12.05$

ለ. $2.4 * \frac{9}{2} = \frac{27}{25}$ መ. $2.4 * 4.5 = 10.8$

20. $6\frac{1}{4} \div \frac{5}{16}$ በዚህ ሂሳባዊ ስሌት ትክክለኛው መልስ የትኛው ነው?

ሀ. 20 ሐ. 25

ለ. 15 መ. 30

*21.* *መሬት* ከፀሐይ ያላት ርቀት 147450000 *ኪሎ ሜትር* ነው። ይህ ርቀት በ10 ርቢ ሲገለፅ ትክክለኛው የትኛው ነው?

ሀ. $14.745 * 10^8$ *ኪሎ ሜትር*

ለ. $1.4745 * 10^8$ *ኪሎ ሜትር*

ሐ. $0.14745 * 10^8$ *ኪሎ ሜትር*

መ. $147.45 * 10^8$ *ኪሎ ሜትር*

22. በሚከተለው መስመራዊ  የእኩልነት ዓረፍተ ነገር የተለዋዋጩ ዋጋ ስንት ነው?

$$መ + 1.25 = 8.75$$

ሀ. 4.5 ሐ. 7.5

ለ. 5.5 መ. 6.5

23. የሚከተለውን መስመራዊ ያለእኩልነትን እውነት የሚያደርገው የ"ቀ" ዋጋ ስንት ነው?

$$ቀ + 12 \geq 20$$

ሀ. 5 ሐ. 7

ለ. 6 መ. 8

24. የሚከተለውን መስመራዊ ያለእኩልነትን እውነት የሚያደርገው የ"ሸ" ዋጋ ስንት ነው?

$$ሸ + 15 \leq 25$$

ሀ. 8 ሐ. 14

ለ. 12 መ. 16

25. የአምስት ደብተሮች ዋጋ 350 ብር ነው። አንድ ተማሪ በ560 ብር ስንት ደብተሮችን መግዛት ይችላል?

ሀ. 6 ሐ. 10

ለ. 8 መ. 12

26. ከዚህ በታች በተሰጠው ግራፍ "ቀ" እና "ሸ" ርቱዕ ወደረኛ ናቸው።




27. ከሚከተሉት ውስጥ የ"ቀ" እና "ሸ" ርቱዕ ወደረኛነትን እውነት የሚያደርገውን ጥንድ ቁጥሮች የተኞቹ ናቸው?

ሀ. (2,10) ለ. (5,25 ሐ. (6,30) መ. (7,45)

28.ከሚከተሉት ውስጥ ኢ- ርቱዕ ወደረኛነትን የሚገልጸው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ. ሁዳ እና ናትናኤል የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: ትምህርታቸውን ጠንክረው ስላጠኑ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል::

ለ. የአስቴር እናት አምስት ሊትር ዘይት ልትገዛ ሱቅ ሄዳ የዘይቱ ዋጋ በጣም ስለጨመረባት ሶስት ሊትር ዘይት ብቻ ገዝታ ተመለሰች::

ሐ. የሰሚራ አባት በትርፍ ሰዓት ለሰራው ሥራ ተጨማሪ ገንዘብ ስለተከፈለው ሰሚራን በዕረፍት ጊዜዋ የተለያዩ መዝናኛ ቦታዎችን አስጎበኛት::

መ. ዮናስ የ6ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ጠዋት ጠዋት አዘውትሮ እስፖርት ስለሚሰራ በሽታን የመከላከል አቅሙን ጨምሯል::

29. ከሚከተሉት ውስጥ ጉርብትና አንግሎችን ያልያዘው የትኛው ነው?




ሀ. < ሀሐለ እና <ለሐመ

ለ. < መሐለ እና <ለሐመ

ሐ. < ሀሐለ እና <መሐሠ

መ. < ለሐሀ እና <መሐለ

30. ከሚከተሉት ውስጥ የጎነ ሦስት ርዝመቶች መሆን የማይችለው የትኛው ነው?

ሀ. 3 ሳ.ሜ፣ 4 ሳ.ሜ እና 5 ሳ.ሜ

ለ. 8ሳ.ሜ፣ 6ሳ.ሜ እና 10 ሳ.ሜ

ሐ. 7 ሳ.ሜ፣ 5 ሳ.ሜ እና 9 ሳ.ሜ

መ. 1ሳ.ሜ፣ 4 ሳ.ሜ እና 6 ሳ.ሜ